# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 7 ቁጥር 2 የካቲት ፲፬ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.


## የካቲት 1966 ዓ.ም. 46ኛ ዓመት

*(የድምፅ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=nhl2Lxei2G0 )*

የካቲት 1966 ዓ.ም. 46ኛ ዓመት ትውስታ፡፡ <<ያ ትውልድ ተቋም>> ከተመሠረተበት ሰኔ 28 ቀን 2004 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚያደርጋቸው አስተዋጽዖች አንዱ ወቅታዊና ታሪካዊ ቀናትን ማስታወስ ነው፡፡ በመሆኑም ለአለፉት 7 ዓመታት ሰባት ቅጾችን አስነብበናል፡፡ ይህ ሲሰላ እስከዛሬ ስለ የካቲት 1966 ዓ.ም. ግብታዊ አብዮት ሰባት ጽሁፎችን አቅርበናል፡፡ በየዓመቱ አንድ ማለት ነው፡፡ የዘንድሮውን መደጋገም እንዳይሆንብን በግጥም የካቲትን አስታውሰናል፡፡ በድምጽም አያይዘናል፡፡ መልካም ትውስታ ለጊዜው የያ ትውልድ አካላት ስንል ለዛሬውና ለአዲስ ትውልዶች ከታሪካችን በጎም ሆነ ደካማ ጎን ትምህርት ትቀስሙ ዘንድ፣ ወደፊት በያ ትውልድ የትግል ታሪክ ላይ ለምታደርጉት ጥናታዊ ምርምርም ሆነ ጽሁፎች ይረዳ ዘንድ እነሆ! ድርሻችንን ብለናል፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን፡ ክብርና ኩራታችን

የሦስት ሺህ ዓመት፡ ዝና ታሪካችን

የማክዳ ሀገር፡ አክሱም ሀውልታችን

የሰለሞን አገዛዝ፡ ሥርወ መንግሥታችን

ሲዋረድ ተጉዞ ከዛጉዌ

ንጉሥ ላሊበላ፡ አብያተ ክርስትያናት

ክብር ለሀገራችን፡ እስትንፋሰ ሕይወት።

ሰለሞናዊ ሥርወ፡ ለይኩኖ አምላክ

ሀገረ መንግሥት ሲተካ

በቆስጠንጢኖስ ዓፄ ዘርዐ ያቆብ

ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት ዳግም ሲሳብ

ሲሸጋገር ተሰገድ ዘር ከወናግ ሰገድ ዓፄ ልብነ ድንግል

እስከ አድማስ ሰገድ ሚስጥሯ ያለው በመንፈስ ኃይል

በፍፃሜ መንግሥት ዓፄ ተክለ ጊዮርጊስ ቀዳማዊ

መንግሥተ ጎንደር፡ ሥርፀ ድንግል

ነበር ጉዞው ተወራራሽ አንጻራዊ ሰላማዊ፡፡

በዚህ ግና አልቀጠለም፡ የየጁ ዘር የመሳፍንት

ተከሰተ በያለበት ሁሉም ልንገሥ ያለበት

ዘመን መጣ፡ ዘመነ መሳፍንት

የራስ ዘመን፡ የራስ መንግሥት

አባ ሴሩ ጓንጉል፡ ራስ አሊ ትልቁ

ከሺህ 7 መቶ 77 እስከ ሺህ 8 መቶ 45

ዘለቀ አሉ እስከ ደጃች አሉላ፡ ራስ ዓሊ ትንሹ

አስቆጠረ ዓመት አሉ 68ት

ተከፋፍሎ ለዝና ሀገር መግዛት

አስተምሮናል ታሪክ ዘመነ መሳፍንት፡፡

አንድ አደርግ ኢትዮጵያን ብሎ ተነሳና

የተዋበች ልጅ የቋራው ካሣ

ብቅ አለ ከኮሶ፡ እያገሳ እንዳንበሳ

ሰባስቲቦል መድፍ አምሮት ቴድሮስ

የስልጣኔ አድማስ፡ ተገልጾለት ጥቅም የመድፍ

አስተከሎ ከጫፍ፡ ከመቅደላ አፋፍ

አንድነትን ገምዶ የቴዎድሮስ ሹርባ

ከኢትዮጵያዊነት ኩርባ

የነጭ ነጫጭባ፡ አድርጎ ምርኮኛ

እጅህን ስጥ ቢሉት፡ እኮ ይሞክረኛ

በድኑን ሰጣቸው፡ የንጉሥ አርበኛ፡፡

ተጽፎ አንብበናል፡ አዎ! ተምረናል

"መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከተ

ፈሪውን አናውቅም ጀግና አንድሰው ሞተ

ማረከን እንዳይሉ ሰው የለ በጃቸው

ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው

ምናሉ እንግሊዞች ሲገቡ ሀገራቸው

ለወሬ አይመቹ ተንኮለኛ ናቸው"

የተባለላቸው ዓፄ ቴዎድሮስ፡ የመቅደላው ኩራት

ትምህርት ሰጥተውናል ከተጠቀምንበት

ሕይወቱን ሰውቶ፡ ኢትዮጵያን እንዳቆማት፡፡

አባ በዝብዝ አራተኛው፡ የመተማው

ለሀገራቸው የተቀሉ፡ ከድርቡሾች ሲታገሉ

ንጉሥ ቢባሉ ድንበር ጠባቂ ልሁን ያሉ

ታሪክ ነውና ሁሌም ይወሳሉ፡፡

ዓፄ ዮሐንስ ተጽፈዋል፡ ኢትዮጵያን ጠብቀዋል

ለልጅ ልጆች አስረክበዋል፡ ታሪክ ለትውልድ አስተላልፈዋል፡፡

ቅኝቱን ሰምተናል፣ ታሪክ ዘግቦታል

"ሚንሊክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፤

ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ጊዜ አበሻ"

አንብበናል፤ አዎ! ተምረናል . . .

እምዬ ምንሊክ የኢትዮጵያ ጋሻ

ዐድዋን ገንብተዋል ያለም ማስታወሻ

የሥልጣኔ አባት፣ መሪ በብልሃት

ሩብ ምዕተ ዓመት፡ ገዝተዋል ኢትዮጵያን በሥርዓት

ያባ ዳኘው ግዛት ያቆሙት መሠረት

ኢትዮጵያ አንድ ናት ብዙ ጎሳ ያላት፣

የቋንቋ ባለሀብት

ይች ናት ሀገራችን፡ ጠላንም ወደድናት

ትኑር ለዘላለም! ብለን ምንጮህላት፡፡

ልጅ ኢያሱ ዘመናቸው፡ የውዝግብ ሂደታቸው

ተሻግሮ ከንግሥት ዘንድ ከዘውዲቱ

ዘመነ ፍፃሜ እስከ ሺህ 9 መቶ 22

እልፈተ ሕይወት፡፡

ተፈሪ አልጋወራሽ ጠቅል ኢትዮጵያ

በ14 ጠቅላይ ግዛት ለሆኑ አርኣያ

"የምንወደውና ሚወደን ሕዝባችን"

ብለው ሲያወድሱ ሰምተናል አይተናል

አባባ ጃንሆይ! ብለን ዘምረናል።

ሥዩመ እግዚአብሔርን አሜን ብለን ሰግደን

ቀና ስንልና ተምሩ ሲገባን

ለካ ግፍ ይሰራል ከእምነቱ ጀርባ

መጠየቅ ጀመሩ ጃንሆይ አባባ፡፡

የዓለም መንግሥታት፣ የአፍሪካ ሕብረት መሥራች ሀገራችን

አባባ ጃንሆይ የሰላሙ መሪ፣ ትምህርት አክባሪ

ትንሽ ተሳሳቱ፡ ከሕዝባቸው ይልቅ ሥልጣንን ወደዱ፡፡

የአምስት ዓመቱ፤ የፋሽት ወረራ

ሸሹ ፈረጠጡ፤ ተብሎ ሲወራ

ድል አረጉ ተብሎ፡ ሲሾም ምድረ ባንዳ

ቁራጡ አርበኛ፡ ሲደረግ የከዳ

"ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝነሽ ተላላ

የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ"

ሲባል መነሻ ነበር ትግል መጠንሰሻ

ይገጠም ጀመረ፡ ከዘውድ ለመሸሻ፡፡

ክራሮች ፉኖ አሉ፡ በገና ጉም ጉም

ቃላት ቅኔ ተፉ፡ አወይ ወርቅና ሰም

ዋሽንቶች አስተከዙ፡ መሲንቆ አቅራራ

የመድረክ ጭፈራ፡ ቃላቶች ዝመራ

ተጨፈረባቸው፡ በቅኔ በዜማ

ንጉሱ ጥሩ አልሰሩም፡ እያለ ሲያቅማማ

ቀጠለ ጉምጉምታው፡ ኽረ እንደው ጉምጉምታ

ክራሩም ዘመረ፡ ከበሮ ቂም መታ

ገጠር አዘመረ፡ እረኛ ዋሽንት ነፋ

ብሶቱን አሰማ፡ ከጫፍ ከተራራ

ጅራፍ አምባረቀ፡ አራሹ አቅራራ

እንደው ዘራፍ የዋ! ፋኖ ተሠማራ

ቅኔም ድምጽ አሰማ፡ የግፉን አዝመራ፡፡

"ተሰቀለ ቢሉኝ፡ ዝናሩ ነው ብዬ"

ተሰቀለ ቢሉኝ፡ ኮፍያው ነው ብዬ

ለካስ በላይ ሁኗል፡ ትልቁ ሰውዬ

ሰምተናል...ሰምተናል...

በግፍ ተሰቀለ፡ ያ ጀግና በላይ

ሀገር ባላስነካ፡ ለንጉሥ ሲሳይ፡፡

ሰምተናል ሲባል፡

"አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ፡ ሰው አማኙ"

ሹመት መስሏቸው፡ ተንጉሡ ሂደው

ለካስ ሸኙት ሁኗል፡ እከወዷያኛው፡፡

የግፍ ሰለባዎች አሳምነው ገብረወልድ፣ ታከለ ሐዋርያት

መቀስቀሻ ነበሩ፡ ለብልሹው ሥርዓት፡፡

"ግርግር" ብለውት ስሙን ለማሳነስ

በ1953 ወርሃ ታህሳስ

ግርማሜ መንግሥቱ ልጆች የንዋይ

እቅዳቸው ከሽፎ ሲሆኑ ተሰቃይ

ደወል ነበር ለዓፄው መንቃት ተሳናቸው፣

ምንም ሳይመስላቸው 13 ዓመት

የካቲት ያዛቸው ድንገት ሳያስቡት፡፡

ጋሻዎች በ10ሺህ፡ ባላባት ሲያዙ

ገበሬው ሲነቀል፡ ሚያመጣው መዘዙ

ማየት ተስኗቸው፡ "ዕድሜ ልክ" ሲገዙ

ድጋፍ ሰጪ ሆነው፡ ገበሬን ሲገፉ

እድሜ እየጨመረ፡ ሲበራከት ግፉ

ወሎ መጣባቸው፡ ረሃብን ይዞ

ያያቸው ጀመረ፡ ሕዝባችን ተከዞ

ሊያከብሩ ሽር ጉድ 80 ዓመታቸውን፡ ሙብራት ይሰቅላሉ ከተማው እንዲበራ

አልሰሙም ይባላል፣ አይሰሙምም ይባላል፡ የረሃቡን ጉዳይ የወሎን መከራ

አንድ ዓመት ቆጥሮ፡ ድንገት ሳያስቡት የካቲት አበራ፡፡

. . .

የካቲት 11 ሺህ 1966 መምህራን ሥራ አቆሙ

ካራት ለማስቀረት የተወጠነውን፡ ሥርዓተ ትምህርት ሴክተር ሪቪውን

ይነሳ ለማለት አድመው ተነሱ

በማኅበራቸው ኢመማ ሥርዓቱን ወቀሱ።

መቼ በዚህ ብቻ የደሞዝ ጭማሪም አክለው ጠየቁ

በወሰዱት አቋም ሳምንታት ዘለቁ።

ነዳጅ ጭማሪውን፡ እጅግ በመቃወም

ታክሲ ነጂዎች፡ ወጡ ካደባባይ ሥራ ላይ በማደም

ወታደሩ በደሞዝ ጭማሪ ፤ ሆነ ከህዝብ ጋር ተባባሪ

ለሕዝብ ብሶት ግባር ቀደም ተሰላፊ ተማሪዎች

አልን “ አትነሳም ወይ አትነሳም ወይ፤ የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ሆይ!”

ተነስ! ተነስ! አልን፣ ደጋግመንም አልን ሕዝብም ተከተለን እውነት ተነሳልን

የካቲት ዘመረች እሆሃ አበባዬ፡ ትግሌ ጠባዬ

ተናወጠ ካምፓስ በመላው ተማሪ

ይበተኑ ጀመር መልዕክተ በራሪ

ኃይሌን ለማዳከም፡ የካቲት በረታች

ግብታዊነቷን፡ አላስነጥቅ አለች

ሥዩመ እግዚአብሔር፡ ቢጮህ ማን ሊሰማ

ተነቃንቋል ዙፋን፡ በየካቲት ዜማ

የካቲት ሕዝባዊ፡ በ14ቱ ግዛት

ጠንከራ ታገለች፡ ያዄውን ሥርዓት

ማ! ሊሰማ ጠ/ሚር አክሊሉ ሀብተወልድ ካቢኔ በተንኩኝ

እንዳልካቸው ቢሉ ኧረ ፋታ ስጡኝ

በየካቲት ግለት ገብተው ከአጣብቂኝ

“ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥን” በትኖ፣ አስተርቶ

ነጎደ የካቲት አጓርቶና አቅራርቶ፡፡

ሴክተር ሪቪው ተሠረዘ፣ ደሞዝ ተጨመረ፣ የነዳጅ ጭማሪ ተነሳ

ቢለፈፍ ቢነገር አልሰማ አለ የካቲት፤ በአብዮቱ ማዕበል ተውጦ እያገሳ

የካቲት ነጎድጓዱ ሄደ ገሰገሠ

መብረቅ ሆነ ከንዱ ለአሮጌው ሥርዓት

የለም ወደ ኋላ በትቅደም መስተዋት፡፡

የካቲት የሥርዓት ለውጥ ጠየቀ፤ አብዮቱ በህዝብ ደመቀ

በህዝብ የለውጥ ግለት፡ የካቲት ህዝባዊ አብዮት

ይታወሳል ዓመት ከዓመት፡፡

ጨፈርን፣ ተሰለፍን፣ አዎ ዘመርን፣ ፈከርን፣

ጮህን፣ እጃችንን ወደ ላይ አወጣን፣ አነሳን

አዎ! ብለን ዘምረናል

“በትግል በመሞት ነው፡ ነፃነት የሚገኘው፡፡”

ስማቸውን አድምቀን ጮኸናል

“ጥላሁን ለምን? ለምን? ሞተ ብለናል

አዎ ዘምረናል “ዋለልኝ ለምን? ለምን? ሞተ፣ ተሰልፈን

አዎ! ጮኸናል “ማርታ ለምን? ለምን? ሞተች” ዘምረናል

ለትግል ኮኮቦች ለዚያ ትውልድ ፈርጦች፡፡

አዎ ጠይቀናል!

ይቅረቡ! ይቅረቡ! ብለናል ይቅረቡ ለፍርድ

የዓጼው ባለሥልጣናት እነ ቢትወደድ፡፡

የወሎ ረሃቡ ሜዳ መዘርገፉ፣ እጅግ ቢዘገንን መከራና ግፉ

ብለናል ይያዙ፣ ለፍርድም ይቅረቡ ባለሥልጣናቱ

ባላባት፣ መኳንንት፣ ሳይቀሩ መሳፍንቱ

ብለናል፣ ብለናል ለእሥር ይዳረጉ

በሰፈሩት ቁና እስቲ ይሰፈሩ፡፡

በወርሃ የካቲት 1966 ይህንን ብለናል

46 ዓመት ይህን ተሸክሟል፣ ዛሬም ይታወሳል፡፡

. . .

ምስጋና ይግባውና፡ የካቲት አብዮት ግዳጁን ተወጥቷል

የዓፄውን ሥርዓት፡ መንቅሎ ጥሎታል

ቀጣዩን ማሳመር፡ የትውልድ አደራ

እኮ ማን ይረከብ? ማነው ባላተራ?

ቆም ብለን ብናይ፡ መሪ አልባው አብዮት፣

የካቲት ይቀዝፋል፡ አቅጣጫው ጠፍቶበት

ወደ ቀኝ ቢማትር፡ ግራንም ቢቃኘው

ተመሪ ሚሻቸው፡ ገና ጅምር ናቸው

በመዳህ ላይ እያሉ፡ የካቲት ቀድሚቸው

ፈጣን ነው ባቡሩ እያዩት ራቃቸው፣ ሄደ አመለጣቸው፡፡

ብቅ አለ ተሸሉ የደርግ ቀንድ አውጣ

ተቀለበ የካቲት ያለምንም ጣጣ፡፡

ያ ሕዝባዊ አብዮት! የካቲት ደመራ

ይነጉደው ቀጠለ በዳሰሳ፣ በደንባራ

አቅጣጫ ሚሰጠው ትግሉን የሚመራ

ለህዝባዊ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቶ የሚያኮራ፡፡

ኃይል አጥቶ ወደቀ ከምርጦቹ ተራ፡ ከወታደር ጎራ

የፖሊስ ሠራዊት፣ ጦር ሃይሎች፣ የክብር ዘበኛ

በአስተባባሪነት ወጥኖ ሲነሳ፣ እያየነው እኛ

ሰኔ 21 ቀን ደርግ ብሎ የሰየመው

ለበትረ መንግሥቱ ድልድዩን ዘረጋው

መስከረም ሁለት ቀን ሺህ 9 መቶ 67

ምሎና አቅራርቶ ያላንዳች አፍረት

"ታሪክ የጣለብኝ" የሀገር አደራ

ማንንም ሳይፈራ፣ እጅግ እያቅራራ

መለያ አንደበቱን ማርሹን አስከትሎ

ከሥልጣን ላይ ወጣ አያ ድቡልቡሎ፡፡

ተብሎም ተለፈፈ "ንጉሱ ከሥልጣን ወርደዋል

በጊዜያዊነት ወታደሩ ይመራል፡፡"

የታሪክ አደራ ተቀባዩ ደርጉ፡

"ኢትዮጵያ ትቅደም"ን ሰንቅሮ ለወጉ

መሰብሰብ፣ መሰለፍ፣ ሥራ ማቆም ሁሉ

ህገወጥ መሆኑን አወጀ ለሁሉ፡፡

ደርግንም እያየን፡ እኛም ትግሉን ቀጠልን

ለመብት ተፈንክተን፣ ታስረን፣ ሮጠን፣ተገድለን. . . መብትን ከተነጠቅን

ብለን ዘምረናል "ትግል ነው መፍትሄው

ሥልጣኑን እስኪያገኝ ላብ አደር ገበሬው፡፡"

እናማ ቀጠልን. . . ትግላችንን ቀጠልን፣ ቀጠልን...ቀጠልን...

ደርግንም ታገልን...ታገልን...ታገልን...

አሁንም እንደገና . . .

ብለን ቀስቅሰናል ጮኸን አስጩኸናል "መሬትን ላራሹ የምትሹ፤ ተዋጉለት አትሽሹ"

ለሚለው ጩኸት ዱላ ተችሮናል፤ ካልቾም ጠልዞናል፡

በጀርባ ተንጋለን "እባክህን"፡ ብለን ተማጽነናል፡፡

ለ"ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ድምጻችንን ብናሰማ

በሞግዚት አስተዳደር ስም፡ በምርጥ መኮንኖች ሥልጣኑ ተቀማ

"ዴሞክራሲያዊ መብት ለሁሉም ያለገደብ" ጩኸታችን

ጥፋት ሁኖ ተከለከልን እንዳንናገር፣ እንዳንጽፍ ተነገረን፣ ተነገረን

እንዳንሰበሰብ፣ እንዳንደራጅ አዋጅ ወጣብን

ማርሽ አጓራብን፡፡

ሰልፍ በሰላም ብናደርግ ለማሰማት ብሶታችንን፣ ጥያቄሃችንን

በጢስ ጋዝ ታፈንን፣ በዱላ ተቀጠቀጥን፣ ወደ ሥር ተጋዝን

ከርቸሌ፣ ማዕከላዊ ተጋዝን፤ "ዳቦ ለተራብ" ብለን በለመንን

ደግመንም አልተውን ፤ "ድሀ ይማር" አልን፣

እኛው ተባረርን፣ ከክፍል ተሠረዝን፣ በፖሊስ ታሰስን

አልተውን፣ አልተውን አሁንም ተሰለፍን፣ በሰላም ታገልን

አነሳን መብትንም ስለመብት ታገልን፣ ስለ መብት ጮክ አልን

"የብሔር/ብሄረሰቦች መብት ይከበር" አልን፡ አዎን አልን፣ ከቶም አልካድን

"የራስን ዕድል በራስ መወሰን"

አንፍራው አልን "እስከመገንጠል"

ደሞ መለስ ብለን ፤ ፃፍን፣ ፈለሰፍን የትግሉ ጡዘቱ ነውና በመደብ፣

ሀብታምና ደሃ፣ ገዥና ተገዥ

ይውደማሉ! ይጠፋሉ! ቡርዠና በዝባዥ

ያኔ ያኔ ....እኩል ስንሆን በኅብረሱታፌ ርዕዮት

ሁሉም ብሄር/ብሄረሰብ ይኖራል ባንድነት

ለምን ይገነጠል ከመጣ እኩልነት በሕብረሰባዊነት

ብለን አድምቀናል፤ አዎ ቀስቅሰናል

ከወቅቱ ርዕዮት ከሶሻሊዝም ጋር አብረን ተጉዘናል፡፡

ጮኸናል ጮኸናል፡ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር ብለናል

በእስላሞች ሰልፍ ላይ ክርስቲያኑ ጮሃል

እምነት የግላችን በሀገር ተሳስረናል፡

ለዚህም ዋጋ እስር፣ ሕይወትም ከፍለናል፡፡

መቼ አላልንም አልን "የሴቶች ጭቆና ድርብ ነው" ብለናል

አንዱ በጾታዋ ሌላውም በመደብ  ከፍ አርገን ጮኸናል

ከማጀት አደባባይ እህቶች፣ እናቶች ወጥተው ተፋልመዋል፡፡

አንቺ ጭቁን እህትዬ ... እህትዬ

ተነሽ ታገይ አያዋጣም ሁሌ እዬዬ

ዝማሬሃችን በየካቲት ይካተታል፡፡

. . .

የካቲት አብዮት በደርጉ መሪነት ገና ዳዴ እያለ

"ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም" ዘምሮ ሳይጨርስ

"አብዮት ያለ ደም እኮ የትም አይደርስ"

ተብሎ ታወጀ ውሳኔ ፖለቲካ

በ60 ሰው ግድያ ሲፎከር ሲያስካካ

የፍትህ ሚዛኗ ሲመዘን፣ ሲለካ

ብለንም ጽፈናል ገና ከጅምሩ ፍትህ ካረከሠ

"ጭፍን ፋሺዝም በኢትዮጵያ ነገሠ"

አዎን አንብበናል "ዴሞክራሲያ ልሳን" ደርጉ አቅጣጫ ስቷል

እኮ አቅጣጫውን ስቷል፤ አብዮት አብቅቷል በደርጉ ተጠልፏል

የ60ዎቹ ደም ዛሬም ፍትህ ይላል፡፡

. . .

ሲታወጅ ብለናል እድገት በሕብረት

"ጋሪው ቀድሞ ታየ ከፈረሱ ፊት"

በዘመቻ ጀምሮ በዘመቻ ያበቃ

እንደግ/ለእድገት  በሕብረት ተብሎ ታወጀ

ተማሪ አስተማሪ ከ10ኛ በላይ

ወንድና ሴት ሳይለይ እንዲዘምት ታዘዘ

ትኩስ ነው አብዮቱ ሁሉም በደስታ

ሊያስተምር ሊያለማ ተገጠር ተጓዘ

ነበርና የቀደመ ጋሪው ከፈረሱ፤

ዓመትም አልሞላው ዘማች ሲመለሱ

በቅድ ያልተመራ ጥናት የሌለው

በጎርፍ ተወሰዱ፣ ተቃጠሉ ሞቱ

ዜና ይዘገባል፤ አንብበን አዝነናል ጋዜጣ በየለቱ

ዋ! ብለናል "ዋ! መሠረት

ሞተሽ መኖር ስታውቂበት

ካንቺው ቤት ነው፤ካንቺ አካላት

እሳት. . . . . .እሳት ያገኘበት

ዳር እስከ ዳር ሕያው እሳት. . ."

አዎ ጽፈናል ዋ! መሠረት

በነታችው አንቂ በ"ጎሕ" መጽሔት፡፡

የካቲት 25 1967 ታወጀ መሬቱ ሆነ ለአራሹ

ቀለጠ ጭፈራው እልልታው አስተጋባ

ነጻ ወጣ ጭሰኛ፣ ገበሬ አፈር ገፊ፤

ተሠበረ ቁልፉ የባላባት ሥርዓት አከተመ ግፉ

ብለን ደግፈናል ብለን ተሳትፈናል፡፡

ግና አልተዘፈቅንም ጥያቄ አቅርበናል

ሕዝባዊ ጥያቄ ምላሽ ይፈልጋል

ተግባራዊ ይሆን ዘንድ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" ከሁሉም የተውጣጣ

መብት ይኑረው ሕዝቡ ዴሞክራሲ ይምጣ

ብለን ከትበናል፤ ወረቀት በትነናል፣ አጥር ላይ ጽፈናል ደርግን ሞግተናል፡፡

መጀመሪያ "መንቃት፣ መታጠቅ፣ መደራጀት" በሚል መፈላሰፍ

ደርግን አላቀፍንም፤ አቅፈን አልተጓዝንም ብለን ሂሳዊ ድጋፍ

አላልንም ይገደብ፤ ዴሞክራሲ ለተራብ ሕዝብ

ፍፁም አልወጣንም ንቃት ስለሌለው፤ ቅድሚያ እናስተምረው

እንደውም ብለናል በሂደት ይማረው፡፡

. . .

ትግላችን ቀጠለ እጅጉንም ፋመ፡

የካቲት ወለደ ለሀገር/ለሕዝብ ያለመ

ነሐሴ 26 በሺህ 9 መቶ 67፡

ኢሕአፓ ታወጀ ትግሉን ለመምራት

የላብ አደር ፓርቲ የትግላችን መሪ

ብለናል ኢሕአፓ ነው! ኢሕአፓ ነው! ሀቀኛ ተጠሪ፤

ነጻነት አብሳሪ፡፡

"ኢሕአፓ ወይም ሞት!" ብለን ፈክረናል

"በትግል መሞት ሕይወት" ዘምረናል

"ፍፁም ነው እምነቴ፡ የትግሉ ነው ሕይወቴ"

ብለን አብስረናል "ለዘመናት፣ በጭቆና ማጥ

በግፍ ሰንሰለት ታስሬ

መብቴን ሳስከብር፣ ጠላትን ልሽር

ተነስቻለሁ ዛሬ

ይኸው ታጥቄአለው ዛሬ

ብለን ተገድለናል ደማችን ተንዠርጓል

በየአስፏልቱ ላይ ኩ.....ል...ል... ብሎ ሄዷል፡፡

1968 ሜይ ዴይ፤ ወጥተን ካደባባይ

እምም አለች ምድር ተናወጠ ሰማይ

የላባደር ፓርቲው ጮሆ ለላብ አደር

ለኢትዮጵያችን ክብር

አልን ይውደም! ይውደም! ይውደም! ፋሺዝም!

የኢሕአወሊ ልጆች ብለን ውጋ በለው

እንደ ሆቺ ሚኒ እንደ ቼኩቤራ

አልነው እራሳችንን "ፋኖ ተሰማራ

በዱር በገደሉ ትግሉን እንድትመራ

በመሪ ድርጅትህ፣ በኢሕአፓ ጥላ ሥር ከአሲምባ ተራራ፡፡"

የትግሉን መፋፋም የኢሕአፓን ጥንካሬ ያዩ ማሌርዶች፣ ያዩ መኢሶኖች፣ ያዩ የወዝሊጎች

ቢያስሩ ቢገርፉ ቢገድሉ ወጣቶች

ቀጠለ እሥሩ ቀጠልን ታገልን ለሕዝብ መንግሥት፣

ለዴሞክራሲ መብት፡፡

ታሥረንም ታገልን፣ ገርፈውም ሲለቁን ትግሉን ተቀላቀልን

የድሉን ቀን ሳናውቅ "ትምህርት ከድል በኋላ" አልን ብለንም አልተማርን፡፡

ብቸኛው ፓርቲያችን ለሥልጣን ሳይበቃ

ቡጊ፣ ቺቺ፣ ሬጌ ድለቃ

ከቶም ላይታሰብ ሕይወት ትግል ሆነ፡፡

ፋሽስትን ማን ይፈራዋል! ገጠምን አነበብን አስነበብን

"የምር ተኳሹን እኛ ስናውቀው፣

ዝናር በትሬን ማን ደባለቀው" ብለን ቀሰቀስን

ኢሕአፓን አሞቅን ከመንደር ጉራንጉር፣
ከፎቁ ከማግ፣ ሜዳ ተራራውን፣ ጋራ ሸንተረሩን
ኢሕአፓ አደረግነው ኢትዮጵያ ምድሩን፡፡
ኤሌክትሪክ ሽቦ ላይ አርማውን ሰቀልነው
ይህስ ምዕታት ነው እንዳላስባልነው
አጥር ግርግዳዎች በኢሕአፓ ታጅበው
ታዳጊ ሕጻናት ሱቃቸው ኢሕአፓ አርገው
እናቶች አባቶች ዲሞ የት አለች ሲሉን እኛም ስንሰጣቸው
እስላም ክርስቲያኑን አብሮ ያታገለ
በኢትዮጵያዊነት የተኮለኮለ
የካቲት ሲነሳ ኢሕአፓ ካልተባለ
የፓርቲ አባወራ ትግል ያስጀመረ
ኢሕአፓ መሆኑ ካልተመሰከረ
እኮ እንዴት ወዴት የካቲት ተዘከረ፡፡
ኢሕአፓ ፍሬው ሲነመራ ሲያሸት አዝመራ
ከቁንጮው ከማማ አረምን አፈራ
ሀ እና ለ የተባለ እንደ ቀላል ጉዳይ
መቋጫ አልነበረው ሲደርስ ሆ እና ሎ ላይ
ፍርሃት፣ ጥርጣሬ መርዛማ ሲስይ
አበቀለ ውስጡ ፈላጊ አስተዋይ፣ ጥበበ ሰናይ
ጥንካሬ፣ አንድነት ትግሉ ሲጠይቅ
እምነት ግራ ገባው ከወዴት ሊወድቅ
ለትግል ሕይውቱ ፍጹም የነበረው
አወይ አሰናካይ ጥርጣሬ በላው
መጓዝ ብቻ ሆነ እደው በዳሰሳ
ከምድር የወጣ የባህር ውስጥ ዓሳ
መዝለል መፈራገጥ ኸረ ታጣ መላ
እጁን ከጭንቅ እሳት፡ እራስ እየበላ

የኢሕአፓ ውዳሴ የአጀማመሩ
ገና መች ተጻፈ ኢሕአፓ ሚስጥሩ
እንደው በየካቲት ይታወስ ለፍቅሩ
ለሰማዕታት ክብሩ፡፡
. . .
ቀጠለ ትግሉ፣ ከውስጥም ከውጭ
ጦርነት አወጀ: ደርግ ሲያረገን ጭጭ፡፡
እኛም ዘመርን ደግመን፣ ደጋግመን
“ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ለአዲስ ሥርዓት ልምላሜ
ፍጹም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ሕይወቴ”
አልን ቃል ገባን፣ ዳግም ተናገርን ቁርጠኛ አቋም ወሰድን፡፡
ፋሺስት ግድ የለውም ለሱ ሀገር ሥልጣኑ፣
ለሱ ሕዝብ ሥልጣኑ
ሰበሰበ የሰው አውሬ መግረፍ፣ ማሰቃየት፣ መግደል የተካኑ
ቀጠለ ተጧጧፈ ቤት ለቤት አሰሳው ወጣት ማሳደድ
እኛም ስንሸሎከለክ፣ ስንሸዋወድ
አግኝተውንም ገለው ሲጥሉን፤ እኛም ተኲሰን ስንከላከል
የትግሉ ሚዛኑ ወደእኛ ያደላው፣
ቁርስ አርጎን ፎከረ መንግሥቱ በተራው
አጥቂ የተባለው ድንፋታ የፋሺስት
ጠርሙስ ከሰከሰ ደም የተሞላበት
እንደ እብድ ውሻ መንግሥቱ ሲያጓራ
መቀየስ አቃተን፡ በባዶቤት ጉራ
የኢሕአፓ መሪ፡ ኮከብ ተወርዋሪ
ወሬውን ሰማነው በገዳይ አብሳሪ፡
አወይ ቅስም ሰባሪ፡ ተስፋዬ ተቀባሪ
ሆንን ተባራሪ፡፡

ቀጠልን ትግሉን “ታጋይ እንጂ ትግል አይሞት”

ሌላም አልን “በትግል መሞት ሕይወት”

ቀጠሉ እነሱም አሰሳቸውን፣ ግድያቸውን. . .፡፡

. . .

ሜይ ዴይ 69 እጅጉን እሪ በይ

ልጆችሽን ገበርሽ ለፋሽስት ሲሳይ

በዓላችን ብለው ሊያከብሩሽ ቢወጡ

ምነው ሰጠሻቸው ደምን ለሚጠጡ

“ሜይ ዴይ የላብ አደሩ ..”. ብለው ሳይጨርሱ

በፋሽስቶች ጥይት የተፈረከሱ፣

የካቲት ወልዷቸው ላንቺ የወደቁ

በፋሽስቶች ጥይት ተለቅመው ያለቁ

ሊያከብሩሽ ሲመጡ በሰላማዊ ሰልፍ

ማንንም ሳይለይ ቢያር ሲርከፈከፍ

ምድር ቀውጢ ሆነች ወላጅ ተረበሹ

ማን ሞተ? ማን ቀረ? አልቀሩ የሸሹ

ማታ ከተኙበት እየተለቀሙ በፋሺስቶች ጥይት ሲቆሉ አደሩ

እጅግ ብዙ አለቁ በየጉራንጉሩ

የካቲት ወልዷቸው ሜይ ዴይ ተዘረሩ፡፡

“ትግል ነው” አንበለው ከዚማ በኋላ

ያበደ ውሻ ነው ሁሉን የሚበላ

መግቢያ መውጫው ጠፍቶ እራስን ለማዳን

በአራቱ ማዕዘን ነጻ ርምጃ ሆኗል፡፡

ማንንም አይምርም ገሎ ይሰወራል

ወጣት የተባለ/ች አሳሩን/ሯን ይበላል

በየመንገዱ ላይ ሬሳው ይጣላል

አመራርም ሚሰጥ መላ ቅጡ ጠፍቷል፡፡

ወደ ዘመድ ቢሸሽ እዛ ቤት ሌላ አለ

ወጣ ሲባል ከከተማ ጸጉሩ ልውጥ ብለው ይከቱናል

እንዴትስ ተደርጎ ኬላው ይታለፋል

ያ ውብ ተስፋችን በጥይት ተከቧል

እያልን ስንጥር፣ ስንታከት “ትግል ለካ ይሞታል”፡፡

በእድገት የተጀመረ የተማሪ ዘመቻ፡

ሊቋጭ ተዘጋጀ በቀይ ሽብር ዛቻ

መጣልን እስር ቤት፣ መጣልን ቀይ ቤት፡

በየበራፋችን፣ በየቄያችን እሬሳ ሊያመርት።

ግርፉ እንዲሰማ፣ ሲገሉ እንዲታወቅ

ለሊቱን በሞላ ሕጻናት ጨምሮ ወላጅን ሲያስቅቅ

ቀይ ሽብር ቃል የለው ይኑር እንደሞተ አይታወስ ይራቅ፡፡

አሞራ አንዣበበ፣ ጅቦች ተጠራሩ

ደርግ የገደለውን የሰው ልጅ ሊቀብሩ

ድንኳን አይተከል ወደ ውስጥ ሲለቀስ

ነጠላ አይዘቀዘቅ ጥቁር አይለበስ

ሁሉም ቤት ለቅሶ ነው ለቅሶ ደራሽ የለ

ባህል ያራከሰ ቀይ ሽብር ብዙ ነው ስብህናን ያስጣለ፡፡

ሙብት ያገኘው ገዳይ እጅግ ተበራክቷል

ጠያቂ የለውም ሁሉም ገዳይ ሁኗል

ቀይ ሽብር ብለውት እውነት ያሸብራል

ታሪክ ይፋረደው ሀገርን አጥፍቷል፡፡

እድለኞች ከእስር ቤት በተአምር ተለቀቅን

ከቀይ ሽብር ያመለጥን ተሰደድን

ሕይወት መጣች እንደገና ልትጠይቀን

እሺ ያለ ተማረላት፣ ደብተር እርሳስ ጨበጠላት

ሥራ ያላቸው እንደሙያቸው ተጓዙላት

ሁሉም ነገር ጨልሞበት ተስፋው በሀገር የተበላ ወደ ስደት አመራላት

አንዳንዶች ውደሚ ያሏትን ሀገር አኑሪኝ ኣሏት፣

እሷም ቂም ሳትይዝ ታኖራለች

ሳትዋጋ ድል አድርጋናለች

ኩሩ ነታችንን ቀምታናለች

ወደድንም ጠላን ገዝታናለች

ምን ይህ ብቻ ለአንዳዶችማ እናት ሁናለች

ምን ይደረጋል አኑራናለች

መቼስ ማል ጎደኒ. . . . .

...

ምን ሰጠሽን የካቲት?

ምን ተማርን ካንቺ ውበት?

ሳንደራጅ፣ ሳንዘጋጅ መጥተሽብን አመለጥሽ

ዛሬስ ዛሬ 46፣ 46 ትልቅ ዓመት አስቆጥረሽ

ስንተራመስ  እኮ ይሰማሽ፡

አትሁኝብን ትውልድ ወቃሽ፡፡

ሀገር ብሄራዊ ክብሯ ተገፎ ሰንደቋ ደብዝዞ

ሃይማኖቷ ተተራምሶ ዘረኝነት ጦዞ

ታሪኳ ተንቋሾ ዜጎቿም ተዋርደው

ህልም ያላቸው አንቀላፍተው

ጎበዛዝት ዳር ተገፍተው

እንዳናጣት ኢትዮጵያችንን

የተደገሰልንን ዋይታችንን፣ ልቅሷችንን፣

እግዚዮታ የሕዝባችን፣ እጅ ማንቀርበብ የናታችን

አድምጠነው በአንድነት፡ ከተያየን በፍቅር ዓይን፣

በመግባባት በቋንቋችን

ከተጓዝን ትኖራለች የእኛ ምድር ኢትዮጵያችን

ለዘላለም ለክብራችን፡፡

ምኞታችን ዛሬም ህያው

የካቲትን አስታውሰነው፣ መጪውንም ስንቃኘው

አቤቱ አምላክ ብሩህ አርገው፡፡

ሕዝባችንን ይቅር ብለህ፣ ቸርነቱ አያልቅብህ

እንለምንህ ብለን በርከክ

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ባርክ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች

የካቲት 1966 ታሪክ ህያው ነው!

የያ ትውልድን አኩሪ ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ ሁላችንም እንተባበር።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> ለያ ትውልድ መታሰቢያነት።

የካቲት 14 ቀን 2012 ዓ.ም. (February 23, 2020)

**Email** : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com,

ስልክ ፡ (703) 300 4302

**Website** http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org